# የዘ ሐበሻ ወይስ የአጀንዳው ቅሌት በኢሕአፓ ላይ ያነጣጠረው?

ከሲራክ የሚድ ዌስቱ

የሌላውን ጽሁፍ የራስ አስመስሎ ማቅረብ በእንግሊዝኛው **ፕሌጅራይዝም** ሲባል ደግሞ የራስ ያልሆነውን ዓርማ(ሎጎ) ያለባለቤቱ ፈቃድ ለሚፈልጉት ጉዳይ መጠቀም(**ፎርጀሪ**) በሌቦች ዓለም የሚደነቅ ሲሆን በጨዋው ሕብረተሰብ ውስጥ ግን ሌባና ዕውቀተ ደሃ አድርጎ ያስገምታል። ትክክል ባይሆንም ለራስ ጥቅም ሁሉቱንም ጸያፍ ድርጊቶች ማለትም ፕላጀሪዝምና ፎርጀሪን መጠቀም አንድ ነገር ሲሆን ሌላውን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ማዋሉ ደግሞ ሌላ ተንኮል ነው፡፡ ሁለቱንም አንድ የሚያደርጋቸው ግን ሁለቱም ጥፋቶች ያውም አስቀያሚ ጥፋቶች መሆናቸው ነው፡፡ ደግመን ደጋግመን ያየነው ብዙ ታላቅ የተባሉ ሰዎች ባንዱ ወይም በሁለቱም ጥፋቶች ተጠቅመው እስከሚታወቅባቸው ድረስ ገነው ሲጋለጡ ግን መቀመቅ መግባታቸውን ነው፡፡ <u>ለዚህ ጽሁፍ ምክኒያት የሆነኝ በዘ ሐበሻ ድህረ ገጽ ላይ ሁለቱም ሌብነት ማለትም ፕላጀሪና ፎርጀሪ በመጠቀም በኢሕአፓ ልሳን ዴሞክራሲያ ላይ የተሰራው ሴራ ነው</u>፡፡

ሰሞኑን ዘ ሐበሻ የተባለው ዋሾ ድህረ ገጽ የኢሕአፓ ልሳን የሆነውን ዴሞክራሲያ ለጥፎ ነበር፡፡ ይህ ድሕረ ገጽ ከጸረ ኢሕ አፓ ጽሁፎች በስተቀር ኢሕአፓን የሚደግፍ ጽሁፍ እንደማያወጣ በሚገባ እረዳለሁና ዴሞክራሲያን በገጻቸው ላይ ሳይ ብደነቅ አይፈርድብኝም፡፡ ጥርጣሬዬ ግን ምንኛ ዕውነት ስለመሆኑ ለማየት ጊዜም አልፈጀም፡፡ ጉዳዩ እንዲህ ነው፡፡ በድሕረ ገጹ ላይ የተለጠፈውን **ዴሞክራሲያ** የሚለውን ርዕስ ስጫነው የዴሞክራሲያና የወክንድ ዓርማዎች ብቻ ብቅ ይላሉ፡፡ ሁለቱም ዓርማዎች የኢሕአፓ ዓርማዎች ናቸው፡፡ ለም የሚል ጥያቄ መጫሩ አልቀረም፡፡ ደግሜ ጽሁፍ አልባ የሆነውን ግን ሁለቱን የኢሕአፓ ዓርማዎች የያዘውን ባዶ ገጽ ስጫነው የታሕሳስ 2007 ዴሞ ቅጽ 40 ቁጥር 3 የሆነው የዴሞክራሲያ ሕትመት 8 ገጾች ያሉትን ድንቅ መልዕክት የያዘው ጽሁፉን አየሁ፡፡ ይህ የዴሞክራሲያ መልዕክት በኢሕአፓ ልሳን ላይ የሰፈረ መሆኑን ከኢሕአፓ ድህረ ገጽ ላይ ቀደም ባሉት ቀናት አግኝቼ አንብቤዋለሁ፡፡ ሁሉም ነገር አንድ ሁኖ ግን አንድ መሰረታዊ ለውጥ ባለቤትነትን አስመልክቶ ይታያል፡፡ **"የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን"** የሚለው "የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ (**ዴሞክራሲያዊ**) ልሳን" በሚል ተለውጦ ነው ዘ ሐባሻ ያወጣው፡፡ ለምን?

**ለምን** የሚለው ጥያቄ መነሳቱ ተገቢ ሲሆን ለምን የሚለው ሲመለስ ግን **ማን** የሚል ጥያቄ ማስከተሉ አይቀርምና ሁለቱን በሚገባ ምላሽ ይፈልጋሉ፡፡ በርግጥ ለምን የሚለው ጥያቄ የጽሁፉ ባለቤት ኢሕአፓ(ዴ) የተባሉትን አንጃ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡ ቀጥሎ የሚጠየቀው ጥያቄ ግን **ማን** ይሆን ይህን የቅሌት የሰራው፡፡ አንጃው? ወይስ ዘ ሐበሻ? ሴራው ከሁለቱ በላይ አይዘልቅም፡፡ ወይ አንጃው ነው ካልሆነም ዘ ሓበሻ ነው፡፡ ወይም ሁለቱም አሲረው የሰሩት ተንኮል ነው ብለን ልናስብ እንገደዳለን።

አንጃው ይህ የኔ ስራ አይደለም ካለና ራሱን ከሴራው ነጻ ለማድረግ ከደፈረ ችግሩ ያለው ዘ ሓበሻ ላይ ሊሆን ነው፡፡ አይደረግም አይባልምና አንጃው ጽሁፉ የኔ ነው ካለ ዘ ሐበሻ ነጻ ይሆንና ጦርነቱ ካንጃው ጋር ይሆንል ማለት ነው፡፡ የኔ መንፈስ የሚነግረኝ ይህን ሴራ የተቃኘው ዘ ሐበሻ የተባለው ድህረ ገጽ ነው፡፡ ድህረ ገጹ የራሱ ያልሆኑ ጽሁፎችን እንደራሱ በማድረግ በድህረ ገጹ በተደጋጋሚ ይለጥፋል የሚሉ ጉምጉምታዎችን ደጋግሜ ሰምቻለሁ፡፡ ይህን የሚያደርገው ምናልባት ድህረ ገጹን ተወዳጅ ለማድረግ ነው የሚል ፈጥኖ ደራሽ ምላሽ መስጠት ይቻል ይሆናል፡፡ ግን የኢሕአፓን ጽሁፍ የአንጃው ጽሁፍ አስመስሎ ማውጣት ለአንጃው እንጂ ለዘ ሐበሻ ምን ጥቀም ጠብ ያደርግለታል? የሚለው ጥያቄ ለጊዜው ሊያሞኝን ይችል ይሆናል፡፡ ሃቁ ግን ዘ ሐበሻ ኢሕአፓን ይጠላል፡፡ ጥላቻው አሳብጦ እንዳያፈነዳው እንጅ የመጥላት መብቱን አከብርለታለሁ፡፡ ድህረ ገጹ በተለይ ኢሕአፓን የሚቃወም ጽሁፍ ለማውጣት ከፈስ ይፈጥናል፡፡ ኢሕአፓን የሚያጥላላ ወይም የሚቃወም ጽሁፍ ቢጠፋ ድህረ ገጹ ራሱ ጽሁፍን ከማዘጋጀት አይቦዝንም።

በጽሁፌ መጀመሪያ ላይ ዘ ሓበሻ ሁለት የኢሕአፓ ዓርማዎችን ማለትም የዴሞክራሲያና የወክንድን ዓርማዎች ያለ ጽሁፍ ለምን መያዝ አስፈለገው? ዓርማዎቹን በመጠቀም አስመስሎ ግን የድርጅቱ ያልሆኑ መልዕክቶችን ለመጻፍ የተዘጋጀ አያደርገውም፡፡ በኔ ግምት ዘ ሐበሻ ጸረ ኢሕአፓ ስራዎችን ለመስራት አስፈላጊውን መሳሪያዎች ያዘጋጀ እንደሆነ ነው የምረዳው፡፡ ካልሆንማ ለምን የድርጅቱ ንብረት የሆኑትን ዓርማዎች መያዝ ፈለገ? እንግዲህ ዘ ሐበሻ ሁለት ጥያቄዎችን ለመመለስ ሊገደድ ነው? አንደኛ ለምን የኢሕ አፓ ሁለት ዓርማዎችን (ዲሞክራሲያና ወክንድ) ያለጽሁፍ ባዶ ዓርማዎቹን ያዘ? ሁለተኛ የዲሞክራሲያ የታሕሳስ እትምን ኦርጂናል የልሳኑ ባለቤት ኢሕአፓን ትቶ ዴሞክራሲያዊ የሚለውን ቃል

በመዶል የአንጃው ለምን አስመሰለው? ብዙ ጥያቄ ጠይቄ መልስ ለመስጠት የምሞክረው የዘ ሐበሻ የሌብነት ቅሌቱን ግልጽ ለማድረግ ነው እንጅ ጥያቄዎቹ መልስ የማይገኝላቸው ሆነው አይደለም፡፡ ከያዝኩት አጀንዳ ለሰከንዶች ልውጣና **"ዘ ሐበሻ በሰሜን አሜሪካ በብዛት ከሚጎበኙ ኢትዮጵያውያን ድረገጾች መካከል 1ኛ ሆነ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ 2ኛ ሆኗል"** የሚል ራሱን የሚያጋግል ዜና ለማቅረብ ሞክሮ ግን ሊገባኝ አልቻለም ስሌቱና እስቲ ስታቲክስ የምታውቁ አስረዱኝ በማለት ዘ ሐበሻ ተመልከቱ ካለን ድህረገጽ ያገኘሁትን ሰንጠረዠ ከታች አስቀምጬለሁ፡

| | AlexAa – Top Ethiopian News & Entertaqinment Websites of 2014 | Global Rank | USA Rank |
|---|---|---|---|
| 1 | Diretube.com | 18,128 | 38,675 |
| 2 | Zehabesha.com (ZEHAB) | 32,786 | 19,722 |
| 3 | Ethsat.com(ESAT) | 46,962 | 47,972 |
| 4 | Ethiomedia.net | 62,112 | 63,044 |
| 5 | Ethiotube.net | 63,567 | 69,678 |
| 6 | Mereja.com | 65,292 | 49,673 |
| 7 | Mahderetena.com | 87,535 | 2nd- Ethiopia |
| 8 | Satenaw.com | 95,442 | 64,674 |
| 9 | ECADF.com | 96,824 | 174,875 |
| 10 | Ethiopianreview.com | 96,857 | 174,875 |
| 11 | EMF | 376,399 | 299,878 |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

በተቻለኝ መጠን በዘ ሐበሻ ላይ የቀረበውን ሰንጠረዥ ሳላበላሽ ለማቅረብ ሞክሬያለሁ ብዬ አምናለሁ። አላጭበረበርኩም፡፡ ግን ትንተናው አልገባኝምና እንዲገባኝ ነው ሰንጠረዡን የገለበጥኩት። በርግጠ በሰንጠረዡ አቀማመጥ ዘ ሐበሻ የተቀመጠው በቁጥር 2 ላይ ነው፡፡ የሰንጠረዡ ትርጉም ጥቂት ቁጥር ያገኙ ከፍተኛ ደረጃ ያገኛሉ ካልተባለ በስተቀር ከቀረቡት 11 ድህረገጾች ብዙ ቁጥር ያገኘው 376, 399 ድምጽ ያለው ይመስለኛል? ከ11 ተወዳዳሪዎች ውስጥ ዘ ሐበሻ 10ኛ የወጣ እንደሆን ነው ቁጥሩ የሚያመላክተው። ሰንጠረዡን መረዳት አቃተኝ ወይስ ይህም ሌላው የዘ ሐሃበሻ ፕላጀሪዝም ወይም ፎርጀሪ ይሆን?

ወደ ጉዳዬ ስመለስ ዘ ሐበሻ ራሱን ንጹ ያድርግ፡፡